# ሀቅ ያንቃል

ከኦርዮን ሞዲ

ሀቅ ባያንቅ ኖሮ  ደከም ያለ የሀቅ ጠረን ያለውንም ውሸት ለማስተናገድ በሞክርን ነበር ። ወይ ነዶ !  አልሆነምና ሀቅን መቀበል እንደ ኮሶ መድሐኒት የግድ የምንጠጣው ሆኖ አለ ።

በመጅመሪያ፡

- ኦሮሞዎች ኢትዮጵያዊ አይደሉም ያለው፤
- ኦሮሞዎች የሃበሾች ቅኝ ተገዢ ናቸው ያለው
- ለመጣው መንግስት ሁሉ መሳሪያ የሆነው፤
- የኦሮሚያ ነጻ መንግስት መቋቋም ብቻ ነው መፍትሄው ያለው፤
- ከሻዕቢያ ጋር ሆኖ የአሶሳን ፍጅት፤ ከወያኔ ጋር ሆኖ የበደኖን እልቂት ያመጣው፤
- ከወያኔ ጋር አብሮ ዘረኝነትን ያስፋፋውን፤
- ከሻዕቢያ ጋር አብሮ ንጹሓንን የገደለውና  ዛሬም ለዚህ ጸረ ኢትዮጵያ ሀይል መሳሪያ የሆነው፤
- የጭፍን ጥላቻ አባወራው

## ኦነግ ተሳስቼያለሁና የተሳሳተ አቅዋሜን ቀይሬያለሁ ትቸዋለሁ ቢል ምንኛ በሀቅ ደስ ባለን ነበር። ግን አልሆነም ።

ኦነግ አቅዋም ቀየረ ፤ መገንጠልን ተወ ስንባል የነበረው በአስመራ የመሸገው ዳውድ ኢብሳ የሚመራው ኦነግ አቅዋም ቀየረ በሚል ነበር። ለተባለው ለውጥ ምንም ተጨባጭ መረጃ አልነበረም። በስሞኑ ግርግር የተቆጣው የዳውድ (ፍሬው) ኦነግ በግልጽ የቀየርነው አቅዋም የለም፤ እንደ ኤርትራና ደቡብ ሱዳን ነጻ መውጣት ነው ግባችን ያለው። ዳውድ ኢብሳ በፖለቲካ አርቆ አስተዋይነት የሚታማ አይደለምና ፍላጎቱ ውድቅ መንግስት (ፌይልድ ስቴት) የሆነችውን ኤርትራን መሆን ወይም ገና ነጻ ወጣሁ ባለች ማዕግስት ህልውናዋ ብልጭ ድርግም እያለ ያለውን ደቡብ ሱዳን ነው ማለቱ የሚጠበቅ ነው። በፈረደበት አማራ ሕዝብ ላይም የዳውድ ኦነግ የከፈተው አጸያፊ ዘመቻም መጠቀስ ያለበት ነው። ይህን በዚህ እናሳርገው።

የዚህ ኪነት አቀነባባሪዎች ወይም ሳህሌ ደጋጎዎች አይደክሜዎች ናቸውና ወይም ክመጀመሪያው የተሰጣቸው ተልዕኮ ኦነግን መከፋፈል ክሆነ ዋናውና ብቸኛው ኦነግ ነኝ ባዩ ካሳየው ብስጭት

መገመት ይቻላል። እነ አይታክቴ ላይ ታች ብለው የወያኔ ጀኔራሎች የነበሩ ግን ወደ ኤርትራ የከዱ ጀኔራሎችን አግኝቷል ። ጀኔራሎቹ ለዳውድ እጅ ነስተው ቢቀላቀሉትም (ኦነግ በውስጡ አጠራጣሪ ግለሰቦችና ወንጀለኞችን ሲሰበስብ የመጀመሪያው አይደለም) ሳይውል ሳያድር ተለይተውታል ። ሁለት የነበረው ኦነግ ዳውድ ቢክድም ሶስት ሆነ ማለት ነው ። ጀኔራል ከማል የተባለው ከዳውድ የተለየው በፖለቲካ አቅዋም ልዩነት ሳይሆን በአካባቢና ምናልባት ሀይማኖትም ሳይሆን አልቀረም (ክርስቲያን ወለጋና አሩሲ እስላም) የሚሉ ቢኖሩም  ሌሎች ደግሞ የቀድሞ የወያኔ ጀኔራሎችን ከዳውዱ ኦነግ የነጠለው ዳውድ አማራ የሚለው ግን መሪው የጉራጌ ተወላጅ (ብርሃኑ ነጋ) ግንቦት 7 የተባለው ድርጅት ነው የሚሉ አሉ። [1]  በዚህም በዚያም በነከማል የሚመራ የኦነግ አንጃ (አንጃ ስም ቅሚያ ዋና የማደናገሪያ ስልቱ ነውና ) ራሱን ኦነግ ብሎ ብቅ አለ ። ይህን አንጃ መማጠን ከተጀመረ ውሎ አድሯል ። ኦነግ ተቀየረ እያልን ነውና እርዱን እንጂ ተባሉ ። በኤርትራ ምይይጥ እንዲሉ ውይይቱ ተጧጧፈ ። አንጃው ከመገንጠል አቅዋሜ ወይ ንቅንቅ አለ ። ምለላው በረከተ ። ቢያንስ አንድ የባዕድ ሀገር በነገሩ ዘው አለ ። ዳውዶች እንደሚሉት ከሆነ መለስ ሲወገድ የአዲስ ኦህዴድነት ቦታ ክፍት መሆኑም ተነገረ። አንጃው ቋመጠ-- ለስልጣን የማያቋምጥ አንጃ ለመሆኑ  በየት ይገኛል ? ከወደ ሎንዶን አንድ የግንቦት 7 መሪ ወደ አስመራ ደጋግሞ አቀና ። ዳውድ ፊት ነሳው ሲባል የአንጃው መሪ (አዎ ቢገርምም እሱም እዚያው አስመራ ነው) ግን ጆሮውን  ሰጠው ። ተንኮሉ ጨሰ ይላሉ የዳውድ ሰዎች በኦሮሚኛ። አንጃው አቅዋሜን ሳልቀይር የቀየርኩ መስዬ  የምታይበት መንገድ ይፈለግልኝ አለ ። ጽሉል ተመሲልካ ወይም እብድ መስለህ ራታቸውን ጨርስባቸው እንደሚለው የትግሪኛ ተረት አንድነትን የደገፍን መስለን ግንጠላን እናመቻች ዘንድ አቀራረቡን ዚቁን ቃኙልን ሲሉ አንጃዎቹ ጠየቁ ። ቅንብሩ ጊዜ ፈጅቶ በአዲሱ አመት (የባዕዳን) በሚኒያፖሊስ ከተማ ብቅ አለ። ዕጹብ ድንቅ ብለው እንዲለፍፉና እንዲጽፉ የተዘጋጁ ክፍሎች ሚኒያፖሊስ የአንድነት ቤተልሄም ሆነች ብለው ዘመሩ። ከዚሁ ቦታ ስብሰባ ኢትዮጵያውያኖች በአንጃው በተጠሩ የአሜሪካ ፖሊሶች መባረራቸውን ግን አንዳችውንም ራሳችውን የአንድነት ደጋፊ ነን ባዮች ሳይጠቅሱ ቀሩ ።

ግንቦቴዎቹ ወደ አቀነባበሩት የሚኒያፖሊስ ጦማር ይዘትና ሚና ከመሄዳችን በፊት እስቲ አንዳንድ ትዝብቶችን ጉዝጓዝ እናድርግ

1. በባዕዳን እርዳታ ግንቦቴዎቹ ሚዲያውን (መገናኛ ብዙሃኑን) በሀገር ቤትም ሊቆጣጠሩ መጣራቸው እየታየ ነው ። ዳዊት ክበደ ሰተት ብሎ አሜሪካ ገባ ። አራያ ተስፋማርያም በተሰደደብት ህንድ ሳይቀር ግድያ ተሞከረበት፤ተሰቃየ ። ዳዊት የሐበሻ ጋዘጣ አዘጋጅ ግንቦቴ ሆን--የኦነግ አንጃ ሀበሾችን ወደ ስብሰባው ጠራ ብሎ ዋሽቶ አምነውት የሄዱት በፖሊስ ሲባረሩ ታዘብን ። በዚህም በዚያም አለን በመድረክ የሚሉት የግንቦቴዎች ወይም የአሜሪካ ቅጥረኞች መሆናችው ምስጢር አይደለም ። የኤሳት ሃላፊ ተብሎ የተሾመው አበባ ገላው (ከ አውሮጳ ተወስዶ በሲአይኤው ስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ የሰለጠነ) የዚሁ ቡድን አካል ነው ። ለኤሳት 40 ሺ ዶላር ክናሽናል ደሞክራቲክ ኢንስቲትዩት አገኝሁላችሁ ባዩ ይህ አበበ ነው።[2] የተባለው ኢንስቲትዩት ደግሞ ለወይዘሪት ብርቱካን የነጻ ትምህርት ክፍያ ያደረገላት የሲአይኤ ተቋም

መሆኑ ይታውቃል ። የተወሳሰበ ይመስላል? አይደለም። ምንጩ አንድ ነው ። አንዱ አንዱን እየጠቀሰ “ የተሰበረ ዜና ” በሚል ኡኡ ይሉብናል ።

2. ይህ “ ጦር ” ነው በዕቅዱ መሰረት የኦነጉ አንጃ ፕሮግራሜን “አሻሻልኩ” (አሜንድ አደረግኩ) ሲል ተዓምር ብለው፤ ኦነግ መገንጠልን እምቢ አለ ብለው በሬ ወለደን ሊያሳምኑን በጋራ የተንጣጡት ። ኩኔታው በአፍ ስተት፤ በእግሪ ሸርተት መሆኑን ለመሸፋፈን ነው፡፤ የነከማል ጦማር ያው የኦነጉ ነጻ ኦሮሚያ አቅዋም መሆኑን ለመሸፈን ።

3. እውን ግንቦቴዎቹ ለኢትዮጵያ ከቆሙ ለምንስ ከኢትዮጵያ አንድነት ሀይሎች ጋር መተባበርን ተቃወምክ ሲባል የግንቦቴው መሪ (ከአህያ የዋለች ጊደር...ተማረች እንደሚባለው ግለሰቡ ጸረ አማራነት እየተናነቀው ነውና!) ጭራሽ የአንድነት ሀይል የሚባል የለም ብሎ ከመካድ አልፎ አሉ የሚባሉትን ዘልፏል ። ለምን?

4. የሚኒያፖሊሱ ጦማር ይዘቱ እንዳይመረመር ለምንስ ግድግዳዎች በዙ?

5. ከማልም ዳውድም አስመራ ከሆኑ የሚኒያፖሊሱ ጦማርና የግንቦቴዎቹ እንቅስቃሴ ሁሉ በሻዕቢያ የተቀነባበረ ይሆን ወይ? ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመቶ ዓመት የቤት ስራ ሰጠሁ ባለ በሰባት ዓመቱ ይህ ህዝብ ለኢሳያስ ራሱ በታታኝ የቤት ስራ ስለሰጠው (ጠብና ጦርነት ከወያኔዎች ጋር) አምባገነኑ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከመራወጥ አርፎ አያውቅም ። ለመሆኑ የራሱን ሕዝብ ከሚያስለቅስና ኢትዮጵያን ከሚጠላ ሀይል ጋር መተቃቀፍ ክህደት ቢባል ያንሰዋል?

ይህን ካልን በኋላ ወደ ጦማሩ እናምራ ። እውን የኦነጉ አንጃ አቅዋም ቀየረ ? ከማል ከዳውድ ተለየ ቢባልም ያው በሻዕቢያ ስር በአስመራ ሁለቱም የኦነግ ዋና መሪ እኔ ነኝ ይላል በሚባለው የሻዕቢያ ጀኔራል ጣዕመ ቁጥጥር ስር ቢገኙም?

*ሀቅ ያንቃል*

*ሁለተኛው ሀቅ.....*

የ ኤኤፍዲ ጊዜ የነበረው ሩጫና ጉራ ከረዩ ትዝ ይላችኋል? የዋሽንግተን ተላሎች ለዳውድ ኢብሳ ቆመው ሲያጨበጭቡና ቪቫ ሲሉ? ግልጽ የሆነው ሰነድ እያለ ያልተጻፈ እያነበቡ ራሳችውን አታለውና ተታለው ለኦነግ (ይቅርታ ሌላ ተገቢ ቃል አላገኘሁም) መጋዣ ሊሆኑ ሲሯሯጡ? ዛሬም ይህንኑ ለመድገም በግንቦቴዎቹ መሪነት ጩሀት በርክቷል ። ትላንት ኤ ኤፍ ዲን ደግፈው ሲጮሁ ከርመው (ተሳስተን ነበር ግን ሳይሉ) ዛሬ ደግሞ ከማል መገንጠልን ተወ ብለው በባዶ ሲባርቁ ይደመጣሉ ፡፤ ሀቁ ግን ውሀ ቢንጡት ውሀ ነው ። ለምክንያት ድመት ሞተች እንዲሉ ይህ ሁሉ ላይ ታች ፤ለመለስ ተኪዎች አጃቢ ተለጣፊ ለማዘጋጀት ሲሆን በ 1983 አሜሪካና እንግሊዝ የሸረቡብንን የግንጠላ ስራ ለመድገም ነው። በምዕራባውያን የተገደለው ጋዳፊ በወቅቱ ይ ህ ራስን ዕድል በራስ መውሰን በሚል ሽፋን በምዕራባውያን የሚገፋው አቅዋም አፍሪካን ለመበጣጠስ የተዘጋጀ ነው ሲል አውግዞ ነበር ። ግንቦቴዎቹ ኢትዮጵያን አይወዱም-- ከርሳቸውና ገንዘብን እንጂ! ለዚህ ደግሞ ምስክር መጥራትም የሚያስፈልግ አይደለም ።

የሴራው አጀማመርና አካሄድ የሚያሳየን ድፍድፉ ከወደ ላንግሌ ቨርጂኒያ (ሲ አይ ኤ) መምጣቱን ነው። በዋና አካሂያጅነት የተመረጠው ደግሞ ጥንትም ከሲ አይ ኤ የሰራውና በተለይም ታሪካዊ ይሆን የነበረውን የሙት ከተማ አድማን ያኮላሸው የግንቦቴዎቹን ዋና መሪ ነው። በቅድሚያ የቅንጅት ክፍፍል ተካሄደ። የግንቦቴዎች ቡድንም ብቅ አለ ። ገንዘብም ጀሌዎችም ተለገሱት። የአስተማሪነት ሽፋንም አገኘ። (ጸረ ኢትዮጵያው አብዱል አባቦራ በተባበሩት መንግስታት መስሪያ ቤት ተቀጣሪነት ሽፋን አይደል ስለላውን የሚያካሂደው?) ። ግንቦቴው ቡድን በሀገር ቤት አባሎቼ ያላቸውን በየጊዜው ከማስበላትና ለወያኔ ጉራና ጥቃት ሰለባ ከማቅረብ ሌላ ምንም የሰራው ቁም ነገር የለም። ምስጢሩን እንኳን መያዝ የሚችል ቡድን አይደለም ። የዛሬ ዓመት የአባላቱ ዝርዝር ስምና ቴሌፎን ቁጥር በይፋ ባልታወቁ ሰዎች ተሰራጨ። ሰሞኑን ደግሞ የግንቦት 7 ን የአውሮጳ ቅርንጫፍ የተቀዳ ስብሰባ የወያኔ አይጋ ፎረም አስራጭቶታል። (ኦነግና ግንቦት 7 በድርጅታዊ መዝረክረክ አንድ ናቸው) ። በዚሁ መንገድ ከቀጠልንም ኦነግ የተባለውም ቢሆን ለሻዕቢያ ተራ ሽብር መሳሪያ ከመሆንና ለወያኔው አመቺ ማስፈራሪያ ከመሆን ሌላ ከዚህ ሁሉ ዓመት የሻዕቢያና ባዕዳን እርዳታ በኋላ ነጻ ያወጣው ስንዝር መሬትም የለ። ቢኖርም እነዳውድ አስመራን ለቀው የሚሄዱ አለመሆናቸውን የሚያውቁ ያውቃሉ።[3] ስለዚህም ሂደቱ ሲጀመር ከግንቦቴዎቹ ሌላ ድርጅት ለአፈር የሚል ዘመቻ ተከፈተ ። የ 500 ዶላር አርበኞች ክስተት መጣ ። ኤሳት የሚባለው የቴሌቪዥን ጣቢያም በ አጭር ጊዜ በወያኔ ታፍኖ በሀገር ቤት መታየቱ ቢያበቃም ([4]) በአሜሪካና ምዕራቦች ገንዘብና ቁጥጥር ስርጭት ጀመረ) ። በአጭር ጊዜ በከተማ ትጥቅ ትግልና አመጽ ወያኔን ልንጥል ነው ብለው ተስፋ ሰጡን ። የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴት ብሎ ጽፎ የወያኔን ዘረኛ ፖለቲካ የደገፈው የግንቦቴዎች ምክትል መሪ ወደ አስመራ መለስ ቀለስን ተያያዘ ። “ ሁሉን ሀይሎች የማስተባበር ” ዕቅድም ይፋ ሆነ ። ይህ ዕቅድም የሻዕቢያን ሙሉ ድጋፍ አግኝቶ እነ ዳውድ፤ አርበኞች ግንባር፤ ዴምህት ወዘተ ሁሉ ከግንቦቴዎች ጋር ተመያየጡ ። የሻዕቢያ ዋና ተልዕኮ የአንድነት ሀይሎችን ለማግለል መሆኑ ግልጽ ሆኖ መጣ። ግንቦቴዎቹም የዳውድ ኦነግ አቅዋም ቀይሯል ብለው እመኑን ጥሪን አስተጋቡ ። አማኝ ጠፋ። ዳውድም የቀየርኩት የለም እያለ ደረቀ ። ኦነግ እንደገና ተከፋፈለ ተባለ ። እሰየው ያለው ክፍል ጥቂት አልነበረም ። የሕዝብ ጥላቻ ያናወዘው ኢብሳ ጉተማ አስታራቂ ልሁን አለ። ግንቦቴዎቹ ተገንጣዮቹ ሊታረቁ ነው ብለው ሲፈነድቁ የሕዝብን ትዝብት አተረፉ ። ወልደጋብር ይሄ ያዋጣል ወይ የሚል የጠፉ ይመስል አቧራው ጤሰ!

ግርግር ለሌባ ያመቻል ነውናም አሁን እየተካሄደ ያለው ጭብጨባ (ከረንት አፌይርስ፤ ቋጠሮ፤ዘሐበሻ፤ አበበ ገላው፤ ወዘተ ወዘተ) ቁም ነገሩ ላይ እንዳናተኩር ለማድረግ ነው።

በቅድሚያ በነ ከማል ቡድን መግለጫ **ያልተባሉትን** ቁም ነገሮች እንጥቀስ--

1. የነ ከማል ቡድን የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም ስንል የነበረው ስህትት ነውና ተተነዋል፤ አርመነዋል አላለም፡

2. የነ ከማል ቡድን የኦሮሞ ሕዝብ የሐበሻ ቅኝ ተገዢ ነው ስንል የነበረው ስህተት

ነውና ትተነዋል፤ቀይረነዋል አላለም፡

## 3. የነ ከማል ቡድን የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ መፍትሔው ተገንጥሎ ነጻ ኦሮሚያን መመስረት ብቻ ነው ስንል የነበረው ስህተት ነውና ትትነዋል፤ ቀይረነዋል አላለም ።

ያልተጻፈ ማንበብ ችሎታው የላችሁም ልንባል እንችላለን ። የሚኔሶታውን ጦማር በእንግሊዝኛ እንጂ በአማርኛ ላላየነውም ልሂቅ አይደላችሁምና አልገባችሁም ልንባል እንችላለን። የሀቅን ጭራ ይዘናልና ግን አንለቅም ። በተሰራጨው የከማል ቡድን መግለጫ ከላይ የተጠቀሱት ቁምነገሮች ጭራሹንም አልተነሱም። ስለዚህም አልተቀየሩም። ተዳፍነው የታለፉትም ተዘንግተው አይደለም--መግለጫው ላይ ግንቦቴዎችም ሻዕቢያም እንደመከሩብት ግልጽና የሚጠበቅ ነውና። አሌ የሚሉ ካሉ የሻዕቢያን አሰራር የማያውቁ ብቻ ናችው። ( የ ኤ ኤፍዲን መስራች የሆላንድ ጉባኤ የኢሳያስ ቀኝ እጅ የሆነው የማነ ገብረአብ የተባለው ሻዕቢያ በቦታው ተገኝቶ መቆጣጠሩን ማስታወስ ይበቃል) ። እውን ኦነግ የተሳሳተና ከሕዝብ የነጠለውን አቅዋም ሊቀይር ቆርጦ ተነስቶ ቢሆን ኖሮ መግለጫው መጀመሪያ ና እምቡጡ ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና መሰረታዊ ጉዳዮች በሆኑ ነበር። ይህ ግን አልሆነም ።

### የነ ከማል ቡድን መግለጫ ምን ይላል?

በተጠና መንገድ የቀረበው መግለጫ በጋራ እንታገል ይላል ። ለምን ግብ? ወያኔን አስወግዶ ፌደራላዊ ሬፑብሊክን ለመመስረት ይላል መግለጫው ። ነጻ ኦሮሚያ ወይም የወያኔን ዘረኛ ፖለቲካ በሚመለከት የተገለጸ ባለመኖሩ እነ ከማል ፌዴራል ሲሉ ፖለቲካዊ ሳይሆን ወያኔ ባደረገው ዓይነት በብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ መሆኑን መገመት ይቻላል ። ባጭሩ የከማል ቡድን “ ሐበሾች አጅቡንና የራሳችንን ባንዲራ የምናውለበልበት ፌዴራል ሬፑብሊክ እንመስርት” ነው እያለን ያለው። ታዲያ ምን አለበት የሚሉ አይጠፉም ። እነዚህ ግን ፖለቲካም ሆነ በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጠው አደጋ ምን እንደሆነ ማወቅ ያቃታችው ናችው። ላብራራ--

1. የወያኔ የጎሳ ወይም የብሄረሰብ ፌደራል አወቃቀር ሀገርና ሕዝብን ክፋፋይና ጎጂ ነው። 20 ረጅም ዓመታት አይተነዋል ።

2. በሻዕቢያ የታጠቀና የተደገፈን ኦነግ ከቦታው ከደረሰ በኋላ ልነቅንቅ ማለቱ ቀላል አይሆንም።

3. የከማል ቡድን የመገንጠልን መንገድ በግልጽ ትችያለሁ እስካላለ ድረስ (ይህም አፋዊ ይሆን ተግባራዊንትን የሚጠይቅ ነው) ጅብ ቢያነክስ ሜዳን እስኪያገኝ ነውና ሁኔታው ሲያመቸው ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚመርጥ መገመት ይቻላል ። ሻዕቢያ ራሱ ባለ ሶስት አማራጭ ሕዝበ ውሳኔ አካሂዳለሁ ካለ በኋላ አስመራ ሲደርስ ንጻነት ወይስ ባርነት የሚል አጉልና የይስሙላ አማራጩን አቅርቦ የፈለገውን እንደፈጸመ አይተናል ።

የከማል ጦማር ፌዴራል ሬፑብሊክ ማቋቋም ካለም በኋላ የዚሁ ሬፑብሊክ ዋና ተልዕኮ

የብሄረሰቦችን የራስ ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማክበርና የህዝብን ውሳኔ ማክበር መቀብል ነው ሲል አስፍሯል ። ያበጠ ይፈንዳ ነው ነገሩ ወይም ብዙሃኑ ቢያነቡም አይገባቸውም ተብሎ ተደምድሟል ማለት ነው። አልሸሹም ዞር አሉ የተባለውም እዚህ ላይ ነው ። ዳውድና ከማል ጠባችው በፖለቲካ አቅዋም ዙሪያ በተከሰተ ልዩነት ላይ አይደለም የሚባለውም ለዚህ ነው ። የግንቦቴዎቹ የሚዲያና ፓልቶክ ጩሀት ሊሸፋፍነው የማይችለው ሀቅ ይህ ነው--ያንቃልም ። ላብራራ----

1. የከማል ቡድን ሆነ የዳውድ ቡድን *የራስን ዕድል በራስ መወሰን መርሆን የሚረዱት በኢትዮጵያ አንድነት ክልል ሳይሆን ሁለም በመገንጠል ውይም ግንጠላን በሚያመቻች ሻዕቢያዊ ስልት ነው* ። በቃላት ሽፍንፍን አቅዋሜን አልደብቅም ያለው የዳውድ ቡድን ግልጽ በሆነ መንገድ ቅኝ ግዛት ነንና ጥያቄው መገንጠል ሳይሆን የግድ ነጻነት ብቻ ነው ብሎናል ። ሀቁን ተናግሮ የመሸበት ማደር ይሏል ይህ ነው ። የከማል ቡድን የልቡ አቅዋም ይህ ነው ግን በግንቦቶቹ ተቃኝቶ ሐበሻ የሚለውን ወገን ማደናገሩን መርጧል ።

2. የከማል ቡድን ፌደራል የተባለው ሬፑብሊክ ሲቋቋምና ምናልባትም በነ ከማል መሪነት የራሱ ጦርና ፓርላማ ያለው የኦሮሚያ ፌዴራል ረፑብሊክ እውን ሲሆን ባለስልጣኖቹ ሬፌሬንደም (ሕዝበ ውሳኔ) እንዲጠራ ያደርጉና (በቀጥታ ወይም በፓርላማ አማካኝነት) ግንጠላን እውን ያደርጋሉ ማለት ነው ።

3. ኦነጎች ስልጣን ሲባሉ ነጻ ኦሮሚያ ያሉትን እርግፍ አድርገው ትተው ለሹመት እንደሚሰለፉ በደርግም ሆነ በወያኔ ጊዜ ያየነው ሀቅ ነውና ነገም ይደገም ይሆናል ብሎ መጠበቁ ስህተት ላይሆን ይችላል ። ኢብሳ ጉተማ ለወያኔ፤ ከማል ለወያኔ አገልግለዋል--ሁሉንም መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም ። የታሪክ ጋቢያቸው ቆሽሿል በአጭሩ ። ይህ ክስተት ቀጠለ አልቀጠለ ግን ብዙ ሚዛን ወይም አንደምታ የለውም ክትግላችን አንጻር ። የከማል ቡድን የዳውድ ኦነግ እንደከሰሰው ለግንቦቴዎቹ ኦሕዴድ ቁጥር ሁለት ሆኖ ቢገኝ ለኢትዮጵያ መከራዋን አይቀንስላትም--ያባብሰዋል እንጂ! መለስ በሌላ ወያነ ተተክቶ ይህንን ሰቆቃ ግንቦቴዎችና እነከማል ቢያጅቡ ሌላ ዙር ትግል ይጠብቅናል ማለት ነው ።

ስለዚህ ከነ ከማል መግለጫ አዲስ አቅዋም ፍለጋ ወይም የነበረው አቅዋም የቀየረ ብሎ ለማመን መነሳቱ ከቁንጫ መላላጫ መፈለግ ነው። ኦነግ (አንድ ሆነ ሶስት) ለ ኦሮሞ ሕዝብ መብት እታገላለሁ በማለቱ ልንቃወመው አንችልም፤ አይገባምም ። ኦነግ በአቅዋሙ ጠቦና ጭፍን ጸረ አማራ ሆኖ ሲገኝ፤ ኦሮሞ በቅኝ ግዛት ስር ነው ሲል፤የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም፤ በግድም መገንጠል አለበት ሲል ግን በዝምታ ልናየው ልንቀበለው አንችልም ። ኦነግ ራሱ በራሱ የመላው ኦሮሞ ሕዝብ መሪና ተወካይ ነኝ ቢልም ብዙሃኑ የሚቀበሉት አይደለም ( አዎ ነው ብሎ ማንም ሳይጠይቀው በይፋ ምስክርነት የሰጠው ግለሰብ ደግሞ በሚያውቁት ግለሰቦች አንድም ዜሮ በተጨማሪም ኮሶ የተባለ ነውና ሚዛን የለውም) ።

ላጠቃል--

ከ ኤ ኤፍ ዲ በባስ ትንኮል ተሸርቦብናል ። ባዕዳኑም ፤ ሻዕቢያም አሉብት ። ይህን ማየት

ያቃተው ኢትዮጵያዊ ሀገሩን ጥፋት እየዳረገ ነው ። ይህ መታወቅ አለበት ። እነግ የከማል ሆነ የዳውድ--የገላሳ በይፋ የኦሮሞን ኢትዮጵያዊነት አምኖ፤ መብትን በኢትዮጵያ አንድነት መሰረት ፈላጊ ሆኖ በይፋና በማያውላዳ መንገድ መገንጠልን መተዉን ቢያሳውቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ-- በመጀምሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ ያለው ኦሮሞዎች ሁሉ-- በደስታ ያቅፉታል፡ ይድግፉታል። መንገዱ ይህ ነው። የግንቦቴዎቹ መንገድ አያዋጣም ። ኤ ኤፍ ዲ ከሸፏል፤ ከስሟል። የሚኒያፖሊሱም ጦማር ውድቅ ይሆናል ። የሕዝብን ፍላጎት አያሟላምና ።

እነ ከማልና ዳውድ የሚኖሩብት ሀገር ያሉ ሰዎች ሲተርቱ እውነትን ግዛት እንጂ አትሽጣት ይላሉ ። ሀቅ ያንቃልና ነው ።